# ሰው መሆን !



ሰው መሆን ፣ ምንድ ነው፣

ምንድ ነው ሚስጥሩ ፣ የሰው ህልውናው፣

ራስህ መልሰው ፣ ላንተው ነው የተጻፈው፣

ሁሌ እየቆዘሙ ፣ እህህ ብቻ ነው፣

እኔ ምን አገባኝ ፣ ብሎ መቀመጥ ነው፣

ከጀርባ ተጣብቆ ፣ በሰው ደም መኖር ነው፣

እኮ ሰው መሆን ፣ ምንድ ነው፣

ምንድ ነው ሚስጥሩ ፣ የሰው ህልውናው፣

በላቡ እያደረ ፣ ድንጋይ መፍለጡ ነው፣

የላባደር ጉልበት ፣ መበዝበዝ መኖር ነው፣

አልገዛም ብሎ ፣ ታግሎ መሞቱ ነው፣

ልክ እንደ ጌታቸው ፣ አፈር መልበሱ ነው፣

ልክ እንደዋለልኝ ፣ አፈር መልበሱ ነው፣

ልክ እንደ ተሰማ ፣ አፈር መልበሱ ነው፣

በሃይ በትግል ነው ነፃነት የሚገኘው፣

ብሎ እየተመመ ፣ እስትንፋስ ማጣት ነው፣

እኮ ሰው መሆን ፣ ምንድ ነው፣

ምንድ ነው ሚስጥሩ ፣ የሰው ህልውናው፣

ባንዳ የባንዳ ልጅ ሆኖ ፣ መቀጠር ነው፣

ዛኒጋባ ሰርቶ ከቆጥ ፣ መስፈሩ ነው፣

ለፍትሕ ርቱእ ፣ ጠበቃ መሆን ነው፣

በጎሳ ተቧድኖ ፣አገርን ማፍረስ ነው፣

አገር አሳንሶ በውጭው ፣ መድመቅ ነው፣

እኮ ሰው መሆን ምንድ ነው

ምንድ ነው ሚስጥሩ ፣ የሰው ህልውናው ?

ይህ ግጥም ለምወደው ለስጋ ወንድሜ ለጌታቸው፣

እንዲሁም ለተሰማ፣ ለትግል አጋሮቹ ለማርታና ዋለልኝ መኮንን ይሁን ወደፊት በሰፊው እጽፋለሁ።

**መይሳው ከምድረ ስዊድን**

**2018-05-18**